## ም ዕ ራ ፍ ፲፫ ሙ ያ ።

ግብጽና ባቢሎን የጥንት ጓደኞችሽ
ወይዛዝሩ ሁሉ ከድሮ የሚያቁሽ
ባልትናሽን ዐይተው በጣም አደነቁሽ ።
ጠላውን ስትጠምቂ ጠጁን ስትጥይው
እንጀራውን ጋግረሽ ወጡን ስትሠሪው
ዓለም ነሆለለ በጣም ገረመው
ባንጐሌ ባሰበው ባሰላሰለው
ብዙ ነገር አለ መልሱን ማላውቀው ።
ፍጥረቱ ሲደነቅ ልቤ ሲገረም
እመ ፍቀጅልኝ ልጠይቅ እኔም ።

**ኢትዮጵያ** አንተ ስትጠይቀኝ ልረዳ ብለህ
መልሱማ ምንገዶ ሳለሁ እናትህ ።
በል ጠይቀኝና ምትፈልገውን
ይዋል ይደር ሳልል ልንገርህ አሁን ።

**ልብ** ጥያቄዬን ሁሉ እየደረደርሁ
እመ ለፈቃድሽ እጅ እነሣለሁ ።
ጌሾና ብቅልን በፊት ጠንስሰሽ
እንኩሮና አብሽሎ ኋላ ጨምረሽ
ጠላን እንድትጠምቂ ማን አስተማረሽ ፤
በርበሬ ለብቻው ምላስ ሲያቃጥል
ላንቃ ሲከነክን ጥቊር ጅንጅብል
ጉንጭን ሲኰመጥጥ ለቀመሰው ሰው
ጐበዝ ያስለቅሳል ጎመን ዘር ፍሬው ።
አብሹን አዝሙዱን ከረሪማውን
ዝቃቅቤ ጤና አዳም የሚያውደውን
ለቃቅመሽ ተጓሮ ከሰፌው ተጋን ።
አዘና ጦስኙን ከዱር ከጫካው
ሰብስበሽ ቀምመሽ ወጡን ስትሠሪው
ዕፁብ ድንቁ ሙያሽ ልቤን ገረመው ።
እንዲያው በጠቅላላው ባነጻጽረው
እማዬ ለሙያሽ ወደርም የለው ።
ወጥሽ ዝነኛ ነው በዓለም የታወቀ

የቀመሰው ሁሉ በጣም ተደነቀ ።
እስቲ ባልትናሽን እመ ልቍጠረው
የወጥሽ ዐይነቱ እጅግ ብዙ ነው ።
መዓዛው ገና ሲያውድ ሰውን የሚሰይ
ደሮ መረቅ ዳቦ አልጫና ቀይ
ዓሣ ምንቸት አብሽ ሽሮ ግብጥ ምስር
ለማያውቁት ሴቶች ነው ታላቅ ምሥጢር ።
እናቴ በጣሙን ሽሮሽ ጣፈጠኝ
የወተት የምጣድ ብትይ ገረመኝ ።
ዱለትና ክትፎሽ በዓለም የታወቀው
አእምሮዬን ማርኮ ሆዴን አስጐመጀው ።
ጕዝጕዞና እንገራ ጣፋጩን ምናሁሬ
ዓለም ያደንቅሻል እያየ ስትሠሪ ።
አጥሚትና ገንፎ ቅንጬውን ለቍርስ
ይዞሽው ስትደርሽ አለው የደስደስ
የጓደኞችሽን ወጡን ብቀምሰው
ባዶ ቀቅል እንጂ ቅመምም የለው ።
ጤፉን አበጥረሽ በወግ አምሰሽ
ፈጭተሽና አቡክተሽ ምጣዱን ጥደሽ
ነጭ እንጀራ ዐይናማ ሰፈፍ የመሰለ
ጋግረሽ ያበላሽው ፍጥረት ግሩም አለ
አሁን በማን አለ ለእህል ዐይን ሚሠራ
ዐይነ በጎ መሳይ ጥሩ ጤፍ እንጀራ ።
ዐይን አለው እንጀራሽ ያውም ዐይነ በጎ
ፈትፍቶ ለመጕረስ በወጥና በርጎ ።
ራብ ገደል ገባ ምሎ በሥሉስ
ቃተኛውን ለብሶ እንጀራ ቢደረስ
አቶ ሥልስ ቍጭ ብሎ በሞሰብ ቢያየው
ጓደኛው እንጀራ በዐይኑ ጠቀሰው ።
ሀብት ላለው ሰውማ የቅቤ ቊብታ
በእንጀራ ሲልፉት ይሰማል ደስታ
እንዲህ ተሰናድቶ ምግብሽን በመላ
ያገኘው ጠረገው ደስ እያለው በላ ።
ምግቡን እየበላ ልብስሽን ቢያየው
የጥበቡ ሥራ በጣም ገረመው ።

በጣሙን ገረመኝ ይህ ሁሉ ሥራሽ
እማዬ ንገሪኝ ማን አስተማረሽ ፤

ኢትዮጵያ — ይኸ ሁሉ ያየኸው ገርሞህ የጠየቅኸኝ
እኔው ፈለሰፍሁት ማንም አልነገረኝ ።
ለዚህም ማስረጃ እንጀራና ጠላ
ጠጅና ፍርንዱስ ሙያዬን በሞላ
ማንም ሴት አታውቀው ጠይቅ ከኔ ሌላ ።
ወተቴን ገፍቼ ቅቤውን ሳወጣ
አይብ አጠራቅሜ ስሠራ መጣጣ
ሠለጠኑ ብለህ ምታደንቃቸው
አጓቱን መግፋቱ እያቃታቸው
ይልጉ ነበረ ወተት ባፋቸው ።

ልብ — ምግቡስ ይሁንና የልብሱን ነገር
እንደምን አድርገሽ ትሠሪው ጀመር ።

ኢትዮጵያ — ጥንት በመጀመሪያ በዕውቀት ሳልነሣ
ቆርበት ነበር ልብሴ አጽፍና ወላንሳ
ላምነትና ጀንዲ ሲያዩት የሚያሳሳ ።
ስላላስደሰተኝ የጥንት ቆዳ ልብሴ
ፈትዬ ለመልበስ አሰብሁኝ ለራሴ ።
አስቤም አልቀረሁ ወደ ቈላ ሂጄ
ጥጤን ተሸክሜ መጣሁ ወደ ደጄ ።
ሸቀጡን ለቅሜ በደንብ አሳስቼ
ሳሰንም ዳምጬ ከፍሬው ለይቼ
ደግሞም ዳመጠውን በደንብ አባዝቼ
ስፈትል እንዳያውክ እጅ ሥራ አግብቼ
ወዲያው እነድፍና አረፋ አስመስዬ
ለድር ሚሆነውን በወግ አመልምዬ
እስበው ጀመረ ሌሊቱን ቊጭ ብዬ ።
አሰናዳሁና የሸማ ዕቃዬን
ሠርቼ ለበስሁኝ መልካም ጥበቤን ።

ልብ — እንዲያ እንዲያ የኔ እናት እንድትከበሪ
በሕዝቡ መካከል ጥበብ ለብሰሽ ኑሪ ።
ፈትልና ወጥሽን ከሰማሁ ባጭር
እባክሽ ንገሪኝ የርሻሽን ነገር ።

ኢትዮጵያ — ግብርናዬንማ እንደምታየው

በሬዬን ጠምጄ ሌት ተቀን ሳርሰው
የሲሳይ መደብር ምንጩም እሱ ነው ።
አርሳለሁ አፍሳለሁ በጣሙን ጠንክሬ
ልጆቼ እንዲጠግቡ እንዲታወቅ ክብሬ ።
ሞፈሩን ቄርጬ ቀንበሩን አርቄ
ድግሮቹን ጠርቤ እርፉንም ሰብቄ
ዕቃዬን አስልቼ በቃንጭርት አንቄ
ሳርስ እውላለሁኝ ባጭሩ ታጥቄ ።
ተልሜ ገምሼ ተርትሬ ሠልሼ
ማሳውን ጉብሱን በጣም አለስልሼ
በአፍለኛ በሮቼ አውጥቼ ጥጋቱን
አብስዬ ጕልጕዬ አጠፋና አረሙን
አበራየውና ማልዳ በወገዜ
ጤፍ እዘራዋለሁ በተመቸኝ ጊዜ ።
ማሽላ ዳጉሣ ሌላም ብዙ እህል
ሥራው ለብቻ ነው ለያንዳንዱ ሰብል ።
ቅንጣቦን ቀንጥቤ አረሙን አርሜ
ጮርቃው ያስደስታል ሳየው ከዳር ቁሜ ።
ዝርዝሩ ያልፍና እሸቱ ሲደርስ
እያሹ ሲበሉት አለው የደስ ደስ ።
እህሌ እንደ ደረሰ አጭጄ ከምሬ
አበራየዋለሁ ባንዱ መንጋ በሬ ።
ያውድማዬ በሬ እንዲዞርልኝ
የሚከተለውን እዘፍናለሁኝ ።
በሬ የሌላቸው ደብሬ የሌላቸው
በሬ በመለመን ያልቃል ጉልበታቸው ።
በሬዬ አንተን አንተን ደብሬዬ አንተን አንተን
እንጀራህን እንጂ አያሳየኝ ሞትህን ።
ዎሀ በሬ ብሎ ጠምዶ ካላረሱ
እንኳን አበዳሪው ይጓደዳል ዋሱ ።
የበሬን እናት የደብሬን እናት
አልጋ ሥሩላት ሸማ ጋርዱላት ።
አቡኑ ንጉሡ ከናጀባቸው
ደብሬ ሆይ አንተ ነህ መከበሪያቸው ።
በሬ ምንታምር ደብሬ ምንታምር ስትወረወር

በኮማ ሞፈር በሚያዝያ ጀምበር
በሬ ምንታምር ደብሬ ምንታምር ።
ለራሴ በልቼ እህሉን የማቀናው
በሬ ባንተ ላይ ነው ደብሬ ባንተ ላይ ነው ።
አዝመራውን ዕየው በሬ ዘወር ብለህ
አንተ ነህ ያረስኸው መሬቱን ቀደህ ።
በሬ የሌለው ሰው ደብሬ የሌለው ሰው
ከልመና በቀር አሁን ምን ተስፋ አለው ።
ለምኖም አያገኝ በየሰው ደጅ
የሰው ዐይን እሳቱ ይጠብሰዋል እንጅ ።
እንደዚህ ያለውን እያንጐራጐርሁ
እህሉን ከገለባ እለየዋለሁ ።
ግብሱን ገብሼ በግራ በቀኝ
አንጣርባለሁኝ እያባነንሁኝ
አጉማስ የሳተውን ጭድና ገለባ
አራግበዋለሁ ገደል እስኪገባ ።
በጣም ጥሩው እህሌ ሰፌድ ማይገባው
ታጥቄ ካውድማ ባንጣርበው ነው ።
እንዲህ ከነገርሁህ የግብርናዬን
ላውጋህ ስለስፌት አድምጥ ነገሬን ።
ሰበዝና አክርማ በጥቢ ነቅዬ
ግራምጣ ነክሬ አለላም አልዬ
ስሰፋ እውላለሁ ቀኑን ቁጭ ብዬ ።
ነገሥታት መኳንንት ታላለቁ ሕዝብ
ሚበላበት ሰፋሁ ቀለምሻሽ ሞሰብ ።
የሞሰቡን እግር ጌጡን ባየኸው
ጥበብ ኩታ መስሎ ሲያምር አበባው ።
የቀድሞ ሳጥኔ ሙዳይ አገልግል
አስተውሎ ላየው እንዴት ይደንቃል ።
ወራንታና ሌማት ላዳንና እንቅብ
ሁሉም በየሥራው ያስደስታል ልብ ።
የእህል ማበጠሪያ ሰፌድና ወንፊት
አለልህ ከቤቴ በጄ የሰፋሁት ።
የስፌቴ ዐይነቱ በጣም ብዙ ነው
በወሬ አይገባህም ዐይተህ ተረዳው ።

ከዚህ በላይ ደግሞ አለኝ ሽክላ ሥራ
በዐይነት በቀለሙ በጣም የሚያኰራ ።
እኔው አስተምሬ ጠቢብነትን
ሰነፍ ይሰድበዋል ትጉሁን ልጄን ።
አቡክቼ ጭቃውን አፈሩን ቈፍሬ
እሠራዋለሁኝ በጣም አሳምሬ ።
ሰባትና ስምንት ዐሥሩን ተፈጅ
ባየሀልኝ ጋኔን ተተክሎ ከደጅ።
በሁለተ-ፈጅ ሳሌ ባራተ-ፈጅ ቢዴ
አቀርብለታለሁ ሲመጣ ዘመዴ ።
ውኃ ምቀዳበት ማድጋና እንሥራ
ደግሞም መጠነኛው ትልቅ ቶፋ ጣራ
ተቈጥሮ የማያልቅ አለው ብዙ ሥራ ።
ማዘሪያና ጥልቂት ዲሎና ጭንቁላ
ልቈጥረው አልችልም ዕቃዬን በሞላ ።
ገንቦና አሳዳሪ ታላቁ መንቀል
ድስትና ሰታቴ ወጭትና አፍላል
ሲተኰስ ብታየው በጣም ይገርማል ።
የምጠጣበቱ አሽፋትና ኮልባ
አጥቤ ሳኖረው ይመስላል አበባ ።
ዋንጫውን አንጥጬ ወርቁንም አንጥሬ
አውለዋለሁኝ ለሥራ ለግብሬ ።
መጠየቅህ ላይቀር ስለብረትም
እነግርሃለሁኝ የሚቀር የለም ።
ብረቱን አንጥሬ ውኃ ሲመስል
እሠራዋለሁኝ ጐራዴ ሾተል ፤
ማረሻና ማጭድ ገለዶ ወገል ።
አንካሴ ሽብዳ የቦ ቀጭን ጦር
ካራና ቢለዋ መጥረቢያ ምሣር ።
ብዙ መሣሪያ አለኝ በጣም የሚደነቅ
እኔው የሠራሁት ከብርና ወርቅ ።
አልቦና ወርቅ አምባር አሽን ክታብ ድሪ
አርጌ እወጣለሁ ስሄድ ወደ ጥሪ ።
ደግሞም ከዚህ በላይ የተማርሁ ነኝ
ብራና ዳምጬ ስጽፍ ባየኸኝ ።

በሕፃንነቴ የምጽፍበቱ
ብዙ ፍልስፍና የደረስሁበቱ
ግዕዝ ነበር ቋንቋዬ የመጣው ከጥንቱ ።
ያወረድሁበቱ ዜማና ቅኔን
ግዕዝ ነበር ቋንቋዬ ሚያኰራኝ እኔን ።
የዛሬው ልጅ ተግቶ ስላልተማረው
ቅኔዮን ምሥጢሬን ቀረ ሳያውቀው ።
ልብ ወለድ መጻሕፍት ብዙ ፍልስፍና
በግዕዝ ጽፌ ነበር እንዲህ ሊቀር መና ።
ምታውቀው ዜማዬ ግዕዝና አራራይ
መወድስ ቅኔዬ ልብ አይበላም ወይ ፤
ልጄ አንዱን ሳያወቀው ከዚህ ሁሉ ሙያ
እንዲያው ነሆለለ በውጭ ገበያ ።

ልብ	እናቴ አትቈጭው ልጅሽን በጥብቅ
ጒርምስናው አልፎ አእምሮውን ሲያውቅ
ወዳንች ይመለሳል ጥበብ ሊጠይቅ ።

ኢትዮጵያ	አማርኛ አውቃለሁ ብሎ የሚያወራ
ግዕዝ ካላወቀ በከንቱ ፍከራ ።
ግዕዝን ላልተማረ ላልተረዳው ሰው
ያማርኛ ምሥጢር መቼም አይገባው ።
ይህኛው ኰርብጿል ትንሹ ጒብል
ያጠናል ሙያዬን ይፈልገዋል ።
አይበላም ይላሉ ገበሬ ሁሉን
ይህን አሽከር ትቼ ላውጋህ ሥራዬን።
የሌላ አገር ግጥም ማይወዳደረው
ልቅሶዬ ቅኔዬ ዘፈኔም ኀብር ነው ።
እናትህን ሚመስል አሁን የት አለና
የሚወዳደረኝ ባንዲር በበገና ።
በዋሽንት በክራር በትልቅ መለከት
አመዛዝነኝ እስኪ ዕይና ስሜወት ።
በጭወታም በኵል ለጤና ጥበቃ
ብዙ ዐይነት ነበረኝ ላለም የሚበቃ ።
ገና ውኃ ዋና ጒግስና ፈረስ
ሱብና ውኃ ርጭት ልዩ ልዩ ኳስ
እንኳንስ ሲሠሩት ሲያዩት ይላል ደስ ።

ኋስ ብዙ ዐይነት አለው ያስፈልጋል ዐቅድ
አቀብሎ ሩጫ አትቈሻመድ ።
ብዙ ዐይነት ስልት አላው ደግሞም ውኃ ዋና
እንጐል ይማርካል ይወስዳል ልቡና
ወርደህ ተመልከተኝ ዐባይና ጣና
ባየህ ስወነጨፍ ስሻገር በመላ
ባሕሩን እየቀደድሁ እንደ ዘንዶ ሁላ ።
የቅምጥ ጭዋታ በጣሙን የደራ
ሠንጠረዥ ገበጣ ቍንጥሽ አካንዱራ
ልቡና ያረካል በጊዜው ሲሠራ ።
እቀምም ነበረ መድኃኒትንም
ቶሎ ለመፈወስ ልጄ ሲታመም ።
ከኮሶ ጀምሬ ለደዌያት ሁሉ
ቀምሜ አሰናዳሁ መድኃኒት በሙሉ ።
እስከ ዛሬ ድረስ በዓለም መድኃኒት
ያልተገኘላቸው ብዙ ሕማማት
ቍምጥና ነቀርሳ የሳምባ በሽታ
አጠፋ ነበረ ሁሉንም ባንድ አፍታ ።

## ጀ ግ ን ነ ት ።

አራት ሺ ዘመን በነጻ ስትኖሪ
በታላቅ ብልሐት ሠራዊት ስትመሪ
ጠላትሽን በኀይልሽ ስታደናግሪ
ተብለሽ አታውቂም አንድ ቀንም ፈሪ ።
ጦርሽን አድርተሽ ጋሻ ሰጉደሽ
ሾተል አገንድረሽ ጐራዴ ታጥቀሽ
በታየሽው ቍጥር እመ ጠላትሽ
ይጨነቅ ነበረ በሩቁ ሲያይሽ ።
ቢመጣም ጠንክሮ አንቺ ወደ አለሽበት
ሊወጋሽ ሊያጠቃሽ ባለው ሁሉ ጉልበት
አንገቱን ከልለሽ በያዝሺው ጐራዴ
ትጥዪው ነበረ እመ ያን ወንበዴ ።
ጋሻሽን ቢይዘው ደግሞም ኋደኛው
ጉረሮውን አንቀሽ በሰይፍ ጨፋሽው ።
አንዱንም በርግጫ አንዱንም በጥፊ

ጨፍልቀሽ ፈጀሽው አንድ ቀን ሳታርፊ
አንደኛው ሲታረድ ሌላውም ሲረገጥ
ያየ ከዳር ቁሞ ነበር ይንቀጠቀጥ ።
ቈራርጠሽ በሾተል ከልለሽ በሰይፍ
ትፈጂው ነበረ አንዳችም ሳይተርፍ ።
በጨሬሽ ተላልመሽ በየቦ ያረስሽው
በሾተል አንሥተሽ በሰይፍ ያበሰልሽው
በክቶ ጭቃ ሲሆን ነፃነት ዘራሽው ።
አንቺ ራስሽ ሠርተሽ ጦርና ጋሻን
ታስጨንቂው ነበር ድሮ ጠላትሽን ።
በዘመናችንም ቅልብልብ ቢመጣ
በገዛ መጣሪያው አሳይተሽ ፋጣ
ብታርገበግቢው መድረሻውን አጣ
መትረየስ ሲዘንም መድፉ ሲወጭፍ
በረድ ጥይት ሲወርድ የእጅ ቦምብ ሲጕርፍ ፤
አእሮፕላን ሲያምም ማቱን እየጣለ
ማርገብገብ ነው እንጂ መሸሽ ወዴት አለ ።
መትረየሱ ሲዘንም መድፉ እንዳያ ቢያጓራ
ደመኛን ብትፈጪው በኮሬ ተራራ
ጀግንነትሽን ዐይቶ ወዳጅሽ ሲኰራ
ጠላትሽ ራደ በጣም ሆዱ ፈራ ።
በየመን በዐድዋ ጥንት የሠራሽው
ጊዜው እየበዛ ትውልድ ሲረሣው
የዛሬው ጀግንነት ዕዩው ሲያድሰው ።
እንደ አንቺ ያለ ጀግና አሁን የት ይገኛል
ያንች ልጅ መሆኔ እመ ያኰራኛል ።
ግርድና ማታውቂ ሁልጊዜ እመቤት
ጕበዝ ባለሙያ ቆንጆና ባልቴት ።

__ኢትዮጵያ__ ባለፈው መፈከር ምንም አይረባም
ፈክሬ ስገባ ማን ነበር ሚቆም ።
ሳቅራራ የሰማ ድምፄን በጦር ሜዳ
ማንም አልነበረ ትንሽ ሚወላዳ ።
ስሽልል ብሰማ በትግሬ ተራራ
የመን ተሸበረች ግብጽም ሆዷ ፈራ ።
ሰላም ከወደድሁኝ ተለውጦ ግብሬ

ይህ ሁሉ አለፈና ታሪክ ሆነ ዛሬ ፡፡
ባርነት ከቀረ የሰው ልጅ ሁል ፀሩ
ሰላምና ፍቅር ልጆቹ ይማሩ ፡፡
ተንግዲህስ ሰላም እመኛለሁኝ
ጦርነት ሰለቸኝ ደምም ከረፋኝ ፡፡

## ምዕራፍ ፲፮ ምዕላደ ቃላት ።

በአማረኛ አጥጋቢ ተመሳሳይ የሌላቸውን በእንግሊዝኛ እንፈታለን ። በመግቢያው እንደገለጥነው ከዚህ በታች የሚገኙት ቃላት የሚያገለግሉ በምዕላደ ቃላትነት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የገቡትን በተራ አንባቢና በሕፃናት ዘንድ ከባድ መስለው የሚታዩትን ለመፍታት ነው እንጂ መዝገበ ቃላት መጽሔት ለመሆን አይደለምና አንዳንድ ዘዬ የማይገባቸው ልጆች ቢኖሩ መዝገበ ቃላቱ እስኪ ወጣ እናት አባታቸውን ይጠይቁ ።

### ሀ. ሐ. ኀ.

ሀኔ — የአዳል ሰው የሚታጠቀው አጭር ጐበጥ ያለ ሁለት ልሳን ያለው የጩቤና የጐራዴ ዘር ።

ሀያሲ — Critic አራሚ (ነቃፊ) ።

ሄስ-ሂስ — Crticism (ነቀፋ ፤ ነቀፌታ) ።

ሀልውና — መኖር ፡ አነዋወር ፡ ኑሮ

ሆማ — ተ. ናደት ተቃ አረህ ሜዳ ፤ እልም ያለው ዝንጀሮ የማይወጣበት የተራራ ሌጦን (Cliff) ።

ሆሄ — እያንዳንዱ ፊደል (Letter) ።

ሐረግ
- ፩) ግንድ ሳይኖረው በዛፍ ወይንም በመሬት ላይ የሚሳበው ሁሉ ሐረግ ይባላል ።
- ፪) በ፩ የተናገርነውን የሚመስል ለጌጥ ተብሎ በመጻሕፍት የሚሳብ (የሚሣል) በመስቀልና በዓምደ ወርቅ በሐውልትም ላይ የሚቀረጽ ነገር ሁሉ ሐረግ ይባላል ።
- ፫) የቤተ ዘመድ ሐረግ ፤ ሳቢያ ፤ ዝምድና ፤ ትውልድ ፤ ወሰን ።
- ፬) በመጽሐፍ ላይ መስመር መስሎ የሚሳበውም ጌጥ ሐረግ ይባላል ።
- ፭) በቅኔ የስንኝ አካፋይ ። በዐረፍተ ነገር ውሥጥ ዐቢይና ንዑስ የሚባል ቅጽል እየተጨመረበት የሚገኝ ራሱን ያልቻለ ጥገኛ ዐ. ነ. ማለት ነው።

ሐራም — እምቢ ። ሐራም አለ፡እምቢ አለ፡አይሆንም አለ፡በነገሩ አልተስማማም፤ ሐራም ተ. አሻፈረኝ እምቢ ፤ ተቃ እሽ፡ምንከፋኝ! ምንቸገረኝ ።

ሐውልት
- ፩) የደንጊያና ከሌላም ማናቸውም ዕቃ ለመታሰቢያ የተሠራ ቅርጽ ።
- ፪) በሁለት ዐምዶች መካከል ያለው ክፍት ቦታ ።

ሐጋይ — በጋ ፤ ከታኅሣሥ ፳፭ እስከ መጋቢት ፳፭ ።

ሕግ
- ፩) ደንብ ፤ ሥርዓት ፤ ዐዋጅ ።
- ፪) አሚን ፤ የመጀመሪያ ምሽት ፤ ድንግልና ።

ሕፅን — ማሕፀን እንደ ዐ ፤ ፀ ፤ ወ ፤ በመሳሰሉት ሆሄያት ያለው ክፍት ሥፍራ ።

ኅላፍ — በመጽሐፍ በስተ ግራ ዳር ያለው ባዶ ቦታ (left margin) ተቃ. ግልየት ።

ኅዳግ　　በመጽሐፍ በስተግርጌ (በታች) ያለው ባዶ ቦታ ።

ኆኅት　　በሆሄና በሆሄ መካከል ያለው ክፍት ሥፍራ ።

## ለ

ለመከከ　　ተ. ሞገሞገ ፤ ቀባ ፤ ለመጠጠ ። ተቃ. ቀረፈ ፤ አረገፈ ፤ አሙካዋን ለም ከካ መጣች ።

ለምድ　፩) የበግ ቃባ ፪ ጐፍላ ያለው ዲያቆናትና መኳንንት የሚለብሱት የክ ብር ልብስ ።

ለሰነ　፩) ተ. አመለጠነ ፤ አፍ አገባ ፤ ለፈፈ ፪) መረገ ።

ለሴ　　አነባብሮና ጉዝጉዞ የምትመስል መደርጀቷ ከዳበ ሳሳ የምትል ከአ ጃና ከስንዴ የምትጋገር ቂጣ ።

ለቆ　　ክረምት ከሰኔ ፳፭-መስከረም ፳፭ ።

ለበቅ　　አርጩሜ ፤ ልምጭ ።

ለበቻ　　የትግል ስልት ፤ በጭኑ አልፎ ኳቻውን ሲይዘው የዚህን ጊዜ ለመሰ ንገር ይመቻል ።

ለኮ　　ከልባብ ጋራ የተየያዘ የበቅሎ መሣሪያ ለመሳቢያ የሚያገለግል ።

ለዘብ　　ወዘብ ፤ ገና ሲቃኝ ።

ለጠብ　　ሰፌድ የሚመስል ቅንፍ የለሽ መጋፊያ ።

ሉህ　　አራት ገጽ ወይንም ሁለት ቅጠል ብራና ፤ ወረቀት ።

ሊቀ ሐመር　　ግዕዝ አማርኛ ነው የመርከብ አለቃ (Captain) ።

ላሜዳ　　አካፋ የሚመስል የእንጨት መሣሪያ ።

ላት　፩) የበግ ጅራት ፪) የካራ ፡ የቢላዎ እጀታ ።

ላንብታ (እፍታ)　　ተ. ቀጠፋ ፤ ለወተትና ለወጥ ገፈታ ነው ። በደንበኛው አማረኛ የወ ተትና የወጥ ላንብታ የጠላ ገፈታ ነው ።

ላይዳ (ላሜዳ)　　የገብስ ማባነኛ ማንካ ።

ላዳን　　ወራንታ ።

ሌባ ጣት　　ነፍጠኛ ጣት ፤ ቅልብልብ ጣት ፤ መጥቀሻ ጣት ።

ልምጭ　　ለበቅ ፤ የዕንጨት ዐይነት ፤ መደቢያ ።

ልቃቂት　　ትንሽ ልቅ ።

ልቅ　　ትልልቅ የሆነ ልቃቂት ።

ልባስ　　(ለቤት) ደንበኛ ያልሆነ ክዳን ፤ ለጊዜው ከዝናብ ለማዳን የተሠራ ለመጽሐፍ የገበር ልብስ ።

ልባብ　　የጭነት ከብት መሸበቢያ ።

ልጨኛ　　ያደረጉለትን የማይረሣ ፡ ብድር መላሽ (ለበጎ) ተቃ የበላበትን ወጭት ሰባሪ ውለታ ቢስ ።

ልፉፍ　　ቅፋፍ ።

ሎሚ ፩) ብርቱካን የመሰለ ጐምዛዛ ፍሬ ።
፪) ጕልበት ላይ (Knee cap) ።
፫) ከጕንጭ ላይ ሎሚ የሚመስለው ጕብታ Cheek bone ።

## መ

መሃል ጣት ትልቅ ጣት ።

መህን ላይና ታች የሚሄደው መምቻ (የሸማኔ መሣሪያ) ።

መለግ ሁራረሸና ገብረጠላ የበቀለበት ጭፍቅ ያለ ዳዋ ጫካ ።

መለከት ቀርነ መለከት ፤ ትልቅ እምቢልታ መሳይ ።

መላላጫ የዶሮ ብልት ።

መልሕቅ የመርከብ ማቆሚያ Anchor ።

መልካ (የወንዝ) ውኃው የሚያሻግርበት በር ።

መሎጊያ የደፍ ይበል ማንሻና መወርወሪያ ።

መሐራ ዘኬ ።

ማሠሮ ጮሮጮ ፤ ማለቢያ ።

መመንጠሪያ ማጭድ የሚመስል ለመመንጠሪያ የሚውል ።

መራመሚያ ብራና የሚዳመጥበት መሣሪያ (ራመመ ካለው ግሥ የወጣ) ።

መረባርብ በሠረገላና በሠረገላ ላይ ቤቱን እንዲያጠነክር የሚሸጋገር እንጨት ።

መረግድ ረጅሙ የጸናጽል አጣጣል ፤ የዕንቍ ዐይነት Emerald ።

መር ረድፍ ።

መርሕ የሚመራ (Principle) ።

መርገፍ ከወርቅ ወይም ከብር የተሠራ ዘርፍ ፤ በቤተ ክርስቲያን የወርቅ ወይም የብር ጥላ ዙሪያ የገመድ ሽርብ መስሎ የሚወርደው ፤ (በተለይ ዘርፍ ሲል ለልብስ ነው Fringe ።

መርግ ናዳ Avalanahe ።

መሲና ተቃ. ሰንጋ ።

መሳፍቆ በለዕንጨት ጉልድፍ ወስፌ ።

መስቲ ማዘሪያ ፤ ከቅል የሚሠራ የሊጥ ማዘሪያ ፤ መቀቢያ ።

መስከምቢያ ተ. መሶፊያ ።

መሽቀቅ ጥብጣብ ።

መቅቢያ ማዘሪያ ፤ መቅቢያ ።

መቀነቻ ከምቢያ ጉስም ላይ የሚውለው ክበብ መጥለፊያ ።

መቀናጠ አንዱ አንድ በሬ አንዱ አንድ በሬ አዋጥቶ አንድ ቀን አንዱ በሁለተኛው ደግሞ ሌላው እያደረጉ ዓመት ላንዱ ማረስ ፤ በገና ጨዋታ የተረፈ ቡድን ዓመት ላንዱ እንደሚመታ ተቃ. ቀንጃ ።

መቀንጠቢያ ቀወሳ ፤ የቅል አንገት ።

መቀዘ ተ. ተከዘ ፤ አሰበ ፤ አወጣ አወረደ ፤ አሰላሰለ ፤ አወላወለ ፤ አመነታ ።

መቃን ከመዝጊያው በላይ ያለው አግድሙ ፤ ተቃ. መድረክ ።

መቂናጥ ከሸማኔ ዕቃ ላይ እንደ መቃጥን ሽቅብና ቊልቊል የምትውለበለብ ።

መቃድ እንደ ቀበቶ ሁኖ የተሠራ ገንዘብ የሚይዝ ቀሽመሬ ።

መቅቢያ ከዕንጨት የተሠራ የሊጥ ማስተካከያ ።

መቅን በቅልጥም ውስጥ የሚገኘው ቅባት Marrow ።

መቈርቈቢያ (ግሥ ቈረቈበ) አጭር የሆነ በትር ርዝመቱ አንድ ክንድ ከዱሽ ጥጃ እንዳይጠባ አራክቢ የሚከለክልበት ።

መቊረጪት መቀስ ።

መባቻ የወር መጀመሪያ ቀን ፤ ልደታ ።

መተለገ መረመረ ፤ ለመተገ ።

መቻያ ወታደር በባለሀገር ቤት ሲመራ ብዙ ጊዜ በዳፈን ምክንያት ።

መናኸሪያ የነጋዴ ማረፊያ ሲሄድ ውሎ የሚሰፍርበት የተወሰነ ዲካ ።

መንሽ ካውድማ ላይ ገበሬው ገለባና ውታሬ የሚያወጣበት ባለጣት ዕንጨት ።

መንዶ ከንተር ከክትክታ የተሠራ አጭር አራት ወይም ስድስት ገጽ ያለው ባለማንጠልጠያ እየተቀባ የሚቀመጥ አጭር ዱላ ።

መንቀል ትልቅ ገንቦ ባለሦስት ጆሮ ፤ ከዚህ ነው «ቈሎ በገልግል ጠላ በመንቀል« የመጣ ።

መንደፊያ ድማት ።

መዋሊት መዋያ የፍትሐት ጣጣ «በመዋሊተ ነፍስ እንኳን ልጅን ይድር ከተዝ ካሩ ውሎ ራቱም አያድር» መነሻው ይህ ነው ።

መከዳ ባለሁለት እጅ ወምበር ።

መዘለጠ መዘዘ ፤ ምዝልጥ ሎጋ መዘዜ ።

መደቢያ ምድብ ፤ ከለበቅ የሚቀጥን ።

መድረክ መዝጊያ የሚቈምበት ደፍ ተ. ቃ. መቃን ።

መድፍ ፩) ሙግድ ፤ ታላቅ ጠብመንጃ ።

መገበሪያ ቅዴታ ።

መጋኛ ፩) ትርፍ አንጀት

መጋፊያ ብራካ የነቀላ አጥንት ።

መግላሊት የሸክላ ወስከምቢያ ።

መጠራረቢያ ትንሽ መጥረቢያ ።

መጠነ ራብዒት ጻጉሜ ፯ ቀን ።

መጢ ተ. ባይተዋር ፤ የሌላ ሀገር ሰው ፤ እንግዳ ደራሽ ውኃ ፈሳሽ ተቃ. ። ባላባት ፤ ባለሀገር ፤ ተወላጅ ፤ ጉልተኛ ፤ ርስተኛ ፤ ዋና ፤ ነባር ።

መጥለቂያ ውኃ መቅጃ ።

| | | |
|---|---|---|
| መጫሚያ | | ጫማ ። |
| መጸው | | በልግ ፤ ግቢ ፤ ከመጋቢት ፳፭ እስከ ሰኔ ፳፭ ፤ ዘመን በልግ ። |
| መጻጕዕ | ፩) | በሽተኛ ፤ ድውይ ። |
| | ፪) | አጭር ፤ ቀጭን ፤ ጥሙዛ ። |
| መጽሔት | | ተ. መስታዋት ፤ ሁለት ቋንቋ የሚያያይዝ መዝገበ ቃላት ። ግዕዝ አማ ረኛ መዝገበ ቃላት መጽሔት ይባላል ። |
| መርሙኝ | | መርሙይ ተ. ልብ ፤ የጨባ ሙርሙኝ ከውስጡ እንደ ብረት የጠነከረ መጥረቢያ የሚመልሰው ክፍል ፤ ተቃ. በከቦክ ፤ ቅርፍት ። |
| ሙግድ | | አከንባሎ ። |
| ማሚጋር | | የላሊበላ ቅጽር ፤ ካብ ፤ እድሞ ። |
| ማማት | | ተ. እሽሙጥ ፤ ዋርዳ ። |
| ማሕፀን | | እንደ ፡ በ ፤ ጠ ፤ ለ ፤ በመሳሰሉት ሆሄያት ያለው ክፍት ሥፍራ ። |
| ማርዳ | | ድብ ፤ ዶቃ ። |
| ማስጠበቂያ | | ምላጩ በድንገት ሲነካ እንዳይተኰስ ቃታውን የሚጠብቅ ። |
| ማሻንብል | | የጅብ መንጋ ፤ ኩታራ (በጥቅል) ። |
| ማታረሪያ | | (መታረሪያ) የደጋን ጀማት መገተሪያ ። |
| ማታ ምድር | | አመሻሽ ። |
| ማኅደር | | የመጽሐፍ ቤት ፤ መደብር ፤ መኖሪያ ። |
| ማነቆ | | ተ. ቃንጭርት ፤ ቃጭል ፤ ማነቂያ ። |
| ማነጣጠሪያ | | የጥይቱን መንገድ ማስተካከያ ። |
| ማንቋፌሎ | | (መንቋፌሎ) ቄላፋ መጥለፊያ ዕንጨት ። |
| ማእቶት | | ጠላ ሲቀዳ የገንቦ ማስቀመጫ ። |
| ማኰስ | | ተ. በከንቱ ደከመ ፤ ማሰነ ፤ ለፋ ፤ ተቃ. አውደለደለ ፤ አውደከደከ ። |
| ማዕዶት | | መሻገሪያ ። |
| ማዞሪያ | | ተ. ወንዝ ለወንዝ ያለ አረሀ ፤ ደልዳላ መሬት ፤ የውኃ ጥግ ሜዳ መመ ለሻ (ለሽሃ ከብት) ከብት የሚውልበት ዲካ ። |
| ማዘቢያ | | የመጫሚያ ማሠሪያ ክር ። |
| ማዘንት | | ክብ ምድጃ ። |
| ማዳመጫ ብረት | | የጥጥ ፍሬ መለያ ። |
| ማዳመጫ ደንጊያ | | የጥጥ ፍሬ ለመለየት የሚያገለግል ደንጊያ ። |
| ማድጋ | | እንሥራ ። |
| ማጀት | | በጎታ የተወሰነ ዕቃ የሚቀመጥበት ቦታ ። |
| ማጠቆ | | እግረ ጥብቅ የሥራ ሱሪ ። |
| ማጠሊያ | | ማንጣረቢያ ። |
| ማፈኛ | ፩) | ቀበቶ ወደላይ እንዳይንከረፈፍ የሚይዝ ፪) ቀጭን ሲፈተል ልቃቂቱ |

| | |
|---|---|
| | እንዳይጐለጐል ከእንዝርቱ ዛቢያ ከልቃቂቱ በሰተግርጌ የሚደግፍ ከጥፍ-ጥሬ የተሠራ ። |
| ምሣር | መጥረቢያ ። |
| ምሰሶ | ከክብ ቤት የሚቆም ትልቅ ውጋግራ ። |
| ምርፋቅ | ተ. ደጅ-ሰላም (የበሩ ሳይሆን መሐራ ሚበላበት) መቀጫ ቤተ ማኅበር። |
| ምርማር | ቀንበር የሚያርፍበት የበሬ ጫንቃ ፤ ገበር ። |
| ምስማክ | (የመጽሐፍ) በሁለት ገጽ መካከል ያሉት ክፍት በታዎች ። |
| ምናሁሬ | ከአንገር ለጥቆ የሚረጋ ወተት ከመታለባቸው በፊት ላሞች የሚሰ ጡት ወተት ፤ ከወለዱ በኋላ ከአራት እስከ ስምንት ቀን ነው የሚገኘው። |
| ምንቸት | በለጀሮ ቶፋ ። |
| ምንዝላት | የቅድመአያት (ቅማት) ወላጅ ፤ የእንጅልሽ ልጅ ። |
| ምኩራብ | የአይሁድ ቤተ ጸሎት ። |
| ምዕላደ ቃላት | ከደብተር ወይም ከመጽሐፍ መጨረሻ የሚያስቸግሩትን ቃላት ጽፎ ማጥኛ ። ለምሳሌ እነዚህ ቃላት እንደ መዝገበ ቃላት ሁነው የተጻፉ በት ይህች ክፍል ምዕላደ ቃላት ናት Vocabolary, glossary ። መዝገበ ቃላት ሁለት ቋንቋ በማያያዝ ሳይሆን ያንዱን ቋንቋ ቃላት በተመሳ ሳይና በተቃራኒ የሚገልጥ መጽሐፍ ነው ። Dictionary. |
| ምድብ | መደበያ ፤ ለበቅ ። |
| ምድር ነጐድ | ወንጭፍ ። |
| ምጎን | ምጣድ ፤ ጽዶሽ ። |
| ሞሀይት | ካቻ ። |
| ሞላሊት | የኳቻ መገናኛ አጥንት ። |
| ሞገሞገ | ተ. ለቀለቀ ፤ ቀባ ፤ ለመከከ ። ተቃ. አራገፈ ፤ እፍ አለ ። |
| ሞገድ | ማዕበል ። |
| ሞጥሚጢት | ሻምላ ፤ ጐራዴ መሳይ ። |
| ሞፌ | ተ. ከፋ ፤ ቀላል ፤ ውኃ ያመጣው በክቢካ ግንድ ። |

## ሠ. ሰ. ሸ.

| | |
|---|---|
| ሠሌዳ | ልዝብ ጠርብ ፤ ብራና ። |
| ሠረገላ | ካንዱ ዐምድ ወደ ሌላው የሚያሸጋግር ተሸካሚ ዕንጨት ። |
| ሠንጠረዥ | ፩) የጭዋታ ዐይነት ። |
| | ፪) በመልከዕ ሠርቶ የሚያሳይ መሥመርና ዘርጋ ያለው ጽሕፈት ። |
| ሠልስትና | ከሦስት ቀን በፊት (ከትላንት በፊት) ። |
| ሠዓሪ | ተ. ሻሪ ተቃ. አክባሪ ። |
| ሰላውዲ | ተ. ወላምጤ ፤ ወስዋሳ ፤ አሻዋኪ ፤ አዋሻኪ ፤ ቢልተኛ ፤ ተቃ. ታማኝ ቀና። |

| | |
|---|---|
| ሰላሌ | የአጓችን አይጥ የያዘው ዐጥንት ። |
| ሰመሬታ | ጠበል በግንቦት ተዘርቶ በነሐሴ መጨረሻና በመስከረም የሚታጨድ ገብስ ። |
| ሰምበ | የቀረር ጓደኛ ። |
| ሰመመን | ታከት ፤ እንቅልፍ ። |
| ሰታቴ | ገልባጣ የሆነ ሰፊ ድስት ። |
| ሰቋሬት | የአፍንጫ ቀዳዳ ። |
| ሰቀሰቅ | ከፍቅ ቀጥሎ ያለው ። |
| ሰቅሳቅ | መናፈሻ ፤ ከመስኮት እናት ከበር እናት ያለው ክፍት ቦታ። ተቃ. ፉቃ. |
| ሰኋ | ተ. ዓመል ፤ እንከን ፤ ጕድለት ፤ ነውር ፤ ታቃ. ውበት ። |
| ሰነገረ | ተ. አንቋለፈ ፤ ጠለፈ (በእግር ወይንም በዕንጨት) ። |
| ሰያብ | ከ፵ - ፷ ያለ ሙሉ ሰው ፤ ደልዳላ ከመጃጃት ያልደረሰ የሕፃንነትን ፅብደት ያለፈ ጉዛም ሽማግሌ ። |
| ሰገባ | አፎት ፤ ማኅደር ። |
| ሰገነት (Balcony) | በእሳተ ከላ ወይንም ፎቅ እንደ ስብሳብ ተቀጥሎ ሚሠራው ። |
| ሰይፍ | ሁለት ልሳን ያለው ቀጥ ያለ የጦር መሣሪያ ። |
| ሰዴቃ | ገበታ ፤ አቄልቋይ ። |
| ሱማያ | የጦር ዛቢያ ፤ የዕንጨት ስም ። |
| ሱቲ | የመጽሐፍ ልብስ ፤ ቅልብልብ ። |
| ሲላ | ተ. ትንሽ ጨሊሊ ፤ ጭልፊት ፤ ጮሌ ፤ ቁቤላ ። |
| ሲር | መጫሚያ (ጫማ) ሚሰፋበት ክር ሲባን ። |
| ሲራክ | የሆሄዎች እግር የሚያርፍበት መሥመር ። |
| ሳሰ | ፍልቅ (ማሳሳት) ። |
| ሳሌ | ቢዴ ። |
| ሳለ አይሰጥ | ተ. የጀርባ አጥንት ፤ አከርካሪ «ሳለ አይሰጥ ሥጋ ዘወር በል ከፊቴ በኋ ሙቶብታል ላላቅሳት ላይቴ» ። |
| ሳጋ | ግድግዳ ሲገደገድ እክፍት ቦታ የሚገባ ዕንጨት ። |
| ሴማ | አርእስት ተከታታይ Series ። |
| ስልት | ተ. ዘዴ ፤ ወሂል ፤ ሙን ። |
| ስሚዛ | ተ. ሰንሰል ። |
| ስቅሰቅ | ከፎቅ ከጥሎ ያለው ። |
| ስብሳብ | የቤት ጥግ ከታላቅ ቤት ተቀጥሎ የሚሠራ ። |
| ስንኝ | በቅኔ ወይንም በግጥም አንድ መሥመር ። |
| ሶርዘ | አምበዛ የሚመስል ዓሣ ። |
| ሶበድአት | ጅራቱ እባብ ወገቡ አንበሳ ከወገቡ በላይ ሰው ሚመስል የአውሬ ምስል። |
| ሽማ | ጃኖ ፤ ጃኖ እዳይቱ ሽማ ልብሱ ነው ። «እንደተሰጣ ሽማ እንደተተከለ ትርሽማ» ። |

| | |
|---|---|
| ሽምገግ | ቱልት ፤ ቂመ ከህን ። |
| ሽረጋኝ | ቃታ. ያዘኝ ። ሽርጋታ ፤ ቃታ. ፤ ጥጋብ ። |
| ሽንኰር | የአልጋ እግር ። |
| ሽንጐበት | ከአገጭ ላይ የሚወጣው ጠጕር (የፍየሉም ይባላል) ። |
| ሻማ | (ሽሚያ) መሻማት ። |
| ሻኛ | ፩) ጥምጥም ከደጋን እጀታ ላይ ሚጠመጠመው ጨርቅ፤የበሬና የግመል ከጫንቃቸው ላይ ያለው ጉብታ ። |
| ሻሁራ | የወርቅ መርገፍ አጫዋች ። |
| ሻፎ | ስለት ያለው የደንጊያ ሽራፊ ። |
| ሽመል | ቀርቀኋ የሚመስል ውስጠ ድፍን ዕንጨት ። |
| ሽርጋታ | ቃታ. ጥጋብ ፤ ዲባ ። |
| ሽርበ | ተ. ወንፈል ፤ ለውኋ ዋና ግን በየፈንታ መጣለቅ ። ተቃ. ሻማ ። |
| ሽሆና | የከብት ጥፍር ። |
| ሽኸር | ተ. ቃ. ሙክት ። |
| ሽክና | የተጌጠ አንኮላ ። አንኮላ ። |
| ሽብልቅ | ተ. ድጅኖ ። |
| ሽብዳ | ተ. አንካሴ ። |
| ሽጕጥር | |
| ሾተል | ቀጭን ጐራዴ ሻምላ ። |

## ረ

| | |
|---|---|
| ረመጨት | ረመጥ የበርሃ ትኵስ አፈርና አሸዋ እንደ ረመጥ ሲፋጅ ይህ የሚበዛው በአድባሆም በረሃ ነው ። |
| ረከቦት | የስኒ ማስቀመጫ Saucer ። |
| ረፋድ | ከሁለት እስከ ፫ ከጥዋቱ ። |
| ረጀት | ከአባት ወደ ልጅ የሚያልፍ ሀብት ጥሪት የአባት ሞቱን አይወዱም ረጀቱን አይሰዱም ። |
| ሬማ | የበግ ግልገል ። |
| ሬም | ተ. ቅፈፍ ። |
| ሬዝ | ከንፈር ላይ የሚወጣ ጠጉር Moustashe ። |
| ራስ ቍር | ራሶች የሚደፉት ራስ ወርቅ ። |
| ራደ | ተ. ተንቀጠቀጠ ፤ ተንዘፈዘፈ ፤ ተንበደበደ ፤ ተርበደበደ ። |
| ርሁብ | ስስ Pamphlet ። |
| ርህብ | ተ. ስፋት ተቃ. ጥበት ። |

ርባን — ከብር ከቈርቈሮ ወይም ከነሐስ አራት ማዕዘን ሁኖ የተሠራ ባለመርገፍ ጌጥ ።

## ቀ

ቀለም — ፩) ከመወርወሪያ የሚገባው ።
፪) Syllable

ቀለበት ጣት — ከትንሽ ጣት ቀጥሎ ያለው ።

ቀለምሻሽ — ሰፋ ያለ የቄሎ መብያ ።

ቀላሽ — መላሽ ፤ መሪ ፤ ቀንዳይ ።

ቀልቤ — ከራስ የሚጠመጠም መቀነት ።

ቀሳ — አንድ ሰው ተስቦ (በሽታ) ፈርቶ የሚሠራው ቤት ።

ቀረሮ — ይላሆ የመሰለ ረዥም ዛፍ ።

ቅርሽ — የእንዝርት ራስ ።

ቀን እኩል — ስድስት ሰዓት ። Noon

ቀሸመር — ጌጤኛ ቀበቶ ።

ቀኖት — ችንካር ።

ቀታሪ — ፩) መታረሪያ ።
፪) የሞፈር አፍንጫ ።
፫) Greenwith

ቀፈድ — የቀንድ ማውጫ ።

ቀስተ ደመና — ፩) የማርያም መቀነት ። ሰባቱን ኅብረ ቀለማት ይዞ በሰማይ የሚታየው ።
፪) ከቆመ ብእሲ በላይ ያለው Arch ።

ቀዘባ — ተ. ለግላጋ ፤ ወጣት ፤ ጮርቃ ።

ቀኝ ቀዬ — ተ. አፍአ ።

ቀወሳ — መቀንጠቢያ ፤ የቅል አንገት ።

ቀጸላ — ፊትን ጨምሮ የሚሸፍን ሻሽ ።

ቁቤላ — ተ. አለብላቢ ፤ ሲላ ተ. ቃ. ፍዝ ድንብዝ ውለናም ።

ቁኒቅል — ቁኒ የሚባል ቅመም መያዣ፤የራስ ቅቤ ማጣፈጫ ሽቱ ቅል፤የአደስ ልቀ።

ቁንን ጭራ — የተቈነነ ጭራ ፤ የመስክ አበባ ።

ቁለጥ — እርበ ።

ቁጨት — መቁጨት ።

ቁብታ — ማሻ፤የቅቤ መምቻ፤ቅቤውን እንደ ተልባ መትቶ ሲበሉት ቁብታ ይባላል።

ቁፍጣን — ማጤሻ ።

ቁንደ በርበሬ — ተፋጅ ሚጥሚጣ ።

ቂቂይ — ተ. ንፋግ፤ ቀብቃባ ተቃ. ቢዘን ፤ ለጋለ ።

| | |
|---|---|
| ቂያማ | (ለውርጭ) በጣም የሚቈምጥ ። |
| ቃሊም | የወንዝ ዳርና ዳር ። |
| ቃንጭርት | ማነቆን ፤ ዕይ ። |
| ቃተኛ | ትኵስ እንጀራ በቅቤ ። |
| ቃታ | ሽርጋታ ። |
| ቄሎ | በተራ ክብት መጠበቅ፤በአንድ የላም ራስ ውስጥ የሚኖር ቅሬ ተረኛ ሲሆን ቄሎኛ ይበላል ። |
| ቅማጭ | ቅጫም ። |
| ቅምጥ | ጭምብቃ ፤ የዐይን አር ። |
| ቅምጫና | አንገታም ቅል ። |
| ቅሣር | የፊደል ማሳመርያ ጌጥ ። |
| ቅሬ | ተ. ምላሰኛ፤ገንበኛ፤ከተሜ፤ዘማ፤አንድነት ሁነው ከብታቸውን የላም ራስ የሚባል አበጅተው የሚጠብቁ ሰዎች ። |
| ቅበላ | ዘወረደ ፤ የጾም መጀመሪያ ፤ አቀባበል ። |
| ቅናት | ምቀኝነት ተቃራኒ ቅንነት ። |
| ቅንት | ተቃ ሆዳም ፤ እንቅብ ሆዱ ፤ አጋሰስ ። |
| ቅንባ | ትንሽ ቅርጫት ። |
| ቅንብ | ተ. እንቡጥ ፤ ቀንበጥ ። |
| ቅንጥ | ጆሮ ጥላ ፤ አናት ። |
| ቅንጭብ | እንደ ቍልቋል ደም የሚወጣው ዕንጨት ። |
| ቅዴታ | መገበሪያ ። |
| ቅድስት | መካከለኛው የቤተ ክርስቲያን ክፍል ። |
| ቅጠል | የሉህ ግማሽ ። |
| ቅጽ | መጠን (Volume) ። |
| ቆቻ | ቀኑን መሉ ማረስ ። |
| ቆመ ብእሲ | የመዝጊያው ግራና ቀኝ ። |
| ቆሬ | ገበቴ ። |
| ቆባ | ተ. ኵንበል ። |
| ቈንጋ | ተ. ቋቢል ። |
| ቍኒ | የስምቡል ዐይነት ፤ የተደቈሰ አደስ ። |
| ቍብቋቦ | ተ. ደንከል ። |
| ቍር | አሁን የእሳት አደጋ ሠራተኞች በራሳቸው የሚደፉት። |
| ቍርባብቻ | የባቄላ ቤት ። |
| ቍንጮጮ | የቤት ፤ የተራራ ፤ የዛፍ ቁንጮ ። |
| ቍንጮ | ሳይላጭ የሚቀር ጠጕር ። |

| | | |
|---|---|---|
| ርባን | | ከብር ከቈርቈሮ ወይም ከነሐስ አራት ማዕዘን ሁኖ የተሠራ ባለመ ርገፍ ጌጥ ። |

## ቀ.

| | | |
|---|---|---|
| ቀለም | ፩) | ከመወርወሪያ የሚገባው ። |
| | ፪) | Syllable |
| ቀለበት ጣት | | ከትንሽ ጣት ቀጥሎ ያለው ። |
| ቀለምሻሽ | | ሰፋ ያለ የቈሎ መብያ ። |
| ቀላሽ | | መላሽ ፤ መሪ ፤ ቀንዳይ ። |
| ቀልቤ | | ከራስ የሚጠመጠም መቀነት ። |
| ቀሳ | | አንድ ሰው ተስቦ (በሽታ) ፈርቶ የሚሠራው ቤት ። |
| ቀረሮ | | ይላሆ የመሰለ ረዥም ዛፍ ። |
| ቅርሽ | | የእንዝርት ራስ ። |
| ቀን እኩል | | ስድስት ሰዓት ። Noon |
| ቀሽመር | | ጌጤኛ ቀበቶ ። |
| ቀኖት | | ችንካር ። |
| ቀታሪ | ፩) | መታረሪያ ። |
| | ፪) | የሞፈር አፍንጫ ። |
| | ፫) | Greenwith |
| ቀፈድ | | የቀንድ ማውጫ ። |
| ቀስተ ደመና | ፩) | የማርያም መቀነት ። ሰባቱን ኅብረ ቀለማት ይዞ በሰማይ የሚታየው ። |
| | ፪) | ከቆመ ብእሲ በላይ ያለው Arch ። |
| ቀዘባ | | ተ. ለግላጋ ፤ ወጣት ፤ ጮርቃ ። |
| ቀኝ ቀዬ | | ተ. አፍአ ። |
| ቀወሳ | | መቀንጠቢያ ፤ የቅል አንገት ። |
| ቀጻላ | | ፊትን ጨምሮ የሚሸፍን ሻሽ ። |
| ቁቤላ | | ተ. አለብላቢ ፤ ሲላ ተ. ቃ. ፍዝ ድንብዝ ውለናም ። |
| ቁኒቅል | | ቁኒ የሚባል ቅመም መያዣ፤የራስ ቅቤ ማጣፈጫ ሽቱ ቅል፤የአደስ ልቅ። |
| ቁንን ጭራ | | የተቈነነ ጭራ ፤ የመስክ አበባ ። |
| ቁለጥ | | እርቦ ። |
| ቁጨት | | መቈጨት ። |
| ቁብታ | | ማሻ፤የቅቤ መምቻ፤ቅቤውን እንደ ተልባ መትቶ ሲበሉት ቁብታ ይባላል። |
| ቁፍጣን | | ማጤሻ ። |
| ቁንደ በርበሬ | | ተፋጅ ሚጥሚጣ ። |
| ቂቁይ | | ተ. ንፋግ፤ ቀብቃባ ተቃ. ቢዘን ፤ ለጋለ ። |

| | |
|---|---|
| ቂያማ | (ለውርጭ) በጣም የሚቈምጥ ። |
| ቃሊም | የወንዝ ዳርና ዳር ። |
| ቃንጭርት | ማነቆን ፤ ዕይ ። |
| ቃተኛ | ትኵስ እንጀራ በቅቤ ። |
| ቃታ | ሽርጋታ ። |
| ቈሎ | በተራ ከብት መጠበቅ፤በአንድ የላም ራስ ውስጥ የሚኖር ቅሬ ተረኛ ሲሆን ቈሎኛ ይባላል ። |
| ቅማጭ | ቅጫም ። |
| ቅምጥ | ጭምብቃ ፤ የዐይን አር ። |
| ቅምጫና | አንገታም ቅል ። |
| ቅሣር | የፊደል ማሳመርያ ጌጥ ። |
| ቅሬ | ተ. ምላሰኛ፤ገንቦኛ፤ከተሚ፤ዘማ፤አንድነት ሁነው ከብታቸውን የላም ራስ የሚባል አበጅተው የሚጠብቁ ሰዎች ። |
| ቅበላ | ዘወረደ፤ የጾም መጀመሪያ፤ አቀባበል ። |
| ቅናት | ምቀኝነት ተቃራኒ ቅንነት ። |
| ቅንት | ተቃ ሆዳም፤ እንቅብ ሆዱ፤ አጋሰስ ። |
| ቅንበ | ትንሽ ቅርጫት ። |
| ቅንብ | ተ. እንቡጥ፤ ቀንበጥ ። |
| ቅንጥ | ጆሮ ጥላ፤ አናት ። |
| ቅንጭብ | እንደ ቍልቋል ደም የሚወጣው ዕንጨት ። |
| ቅዴታ | መገበሪያ ። |
| ቅድስት | መካከለኛው የቤተ ክርስቲያን ክፍል ። |
| ቅጠል | የሉሀ ግማሽ ። |
| ቅጽ | መጠን (Volume) ። |
| ቆቻ | ቀኑን መሉ ማረስ ። |
| ቆመ ብእሲ | የመዝጊያው ግራና ቀኝ ። |
| ቆሬ | ገበቴ ። |
| ቆባ | ተ. ኵንበል ። |
| ቈንጋ | ተ. ቋቢል ። |
| ቍኒ | የስምቡል ዐይነት፤የተደቈሰ አደስ ። |
| ቍብቋበ | ተ. ደንከል ። |
| ቍር | አሁን የእሳት አደጋ ሠራተኞች በራሳቸው የሚደፉት። |
| ቍርባብቻ | የበቈላ ቤት ። |
| ቍንጮጮ | የቤት፤ የተራራ፤ የዛፍ ቁንጮ ። |
| ቍንጮ | ሳይላጭ የሚቀር ጠጉር ። |

| | |
|---|---|
| ቀኁንዶዶ | ክንቃት ። |
| ቀኁግ | ጨሎቃ ። |
| ቀኁጫን | ተ. ንዴት ፤ ቀኁጣ ፤ ግምጫ ። |
| ቋንጢ ወንበር | ሦስት እግር ያለው ክብ ጐድጓዳ መቀመጫ ። |
| ቋቢል | ቄንጋ ። |
| ቋንጣ | ፩) ተዘልዝሎ ተሰቅሎ የደረቀ ሥጋ ፪) ከእንዝርት አናት ላይ የጐመን ዘር ባላ ወይንም ከመዳብ የተሠራ ሲፈተል መጥለፊያ ሚሆነው ። |
| ቋጫ | የስፌት ማሠሮ ። |

## በ

| | |
|---|---|
| በረሃ | ውኃና ሰው የሌለበት ቦታ ። |
| በስታ | ወዲያ ፤ ከነገ በስቲያ ፤ ከትናንት በስቲያ ። |
| በሬ አድክም | የፈጸምን ማዕዶት ፤ ሕማማት አልቆ መጀመሪያው ሥራ ። |
| በትረ ሙሴ | በበረሃ የሚገኝ ስድስት ገጽ ያለው በትር ። |
| በቀቀን | ተናጋሪ አፍ Parrot |
| በትር | በደንብ ተለብልቦና አምሮ የተሠራ ከዱላ የቀጠነ ። |
| በገ-ፈጅ | አንድ በግ ሊያሠራ የሚችል ድስት ። |
| በጋ | ሐጋይ ከታኅሣሥ ፳፫ እስከ መጋቢት ፳፫ ። |
| ቡሪ | የቄላ ሥር ። |
| ቡይት | ትንሽ ጥልቂት ወይም ቶፋ ። |
| ቢተዋ | የልብስ ዐይነት ። |
| ቢዘን | ተ. ለጋስ ተቃ ንፉግ ። |
| ባልጭት | ብልጭት ። |
| ባለቀ | ተ. ጐረመሰ ፤ ለዓቅመ አዳም ደረሰ ። |
| ባጥ | ተ. ጣራ ። |
| ባሕረ ሽሽ | Tide ባሕሩ ጥሎት የሄደ ። |
| ቤተ ማኅበር | መገናኛ አዳራሽ Meeting hall; lecture hall ። |
| ቤተ ሞገስ | ከሸክላ የተሠራ ከቤቱ ቍንጮ ላይ የሚውል ። |
| ቤተ ብለኔ | መታጠቢያ ቤት Bath room (የውሽባ ቤት) ። |
| ቤተ ተውኔት | የትያትር ቤት ። |
| ቤተ አስተርእዮ | የኤክስፓዚሲዮን ቤት ። |
| ብራቅ | መብረቅ ፤ ቡላድ ። |
| ብርገግ | ብራቅ ። |
| ብርኵማ | እጅ ያለው ትራስ ። |
| ብሰክቲ ብስክት | የመጀሪያው ሥጋ ትል Microbe ግሥ በሰከተ ፤ መትላት ጀመረ ፤ ተነፈገ ። |
| ብሶት | ተ. ችግር ተቃ ድልወት ። |

| | |
|---|---|
| ቦይና | እንደሙዝዬ ያለ የሥር ምግብ ። |
| ቦለታ | ከብረት የተሠራ በድሮ ዘመን የሚያገለግል መንጆ ። |
| ቧሂት | አውሎ ነፋስ ። |
| ቧሻት | የበሰበሰ ፤ አዛባ ፤ እበት ተቃ ኩበት ። |
| ቧዴ | ሳሌ ። |

## ተ. ቸ.

| | |
|---|---|
| ተመስጠ | ተ. አፍ ተልብ ሁኖ ባንድ ሥራ መጨለጥ Meditation ። |
| ተረን | ኮለል ። |
| ተረከዝ | ተ. ኩማ ። |
| ተረጨረጨ | እየተበሳጨ አለቀሰ ። |
| ተሲዓት ተስዓት | ዘጠኝ ሰዓት ። |
| ተሰባ | ተ. ገባ ፤ ተረዳ ። |
| ተትመከመከ | ቃመገ ፤ ለጢስ ተትጎለጎለ ። |
| ተነፋነፍ | ሰፊ የቄስ ሱሪ ። |
| ተንቀዠለለ | ተ. ነሆለለ ፤ ነፈለለ ። |
| ተቀጣጥዬ | ከካያ አራት ዓመት በኋላ የሚወጣ ጥርስ ፤ ተንቀጣጥዬ ። |
| ተንጠረበበ | ተ. ኮራ ፤ ሞላ ። |
| ተንበደበደ | ተ. ፈራ ፤ ተንቀጠቀጠ ። |
| ተቆነነ | ተ. ተቈባጠሰ ፤ ተጀነነ ። |
| ተወላደፈ | ቱ. ተጎላደፈ ፤ ተንገደገደ ። |
| ተወራከበ | ተ. ተነቃረከ ። |
| ተውኔት | ተ. ጭዋታ ፤ ትያትር ። |
| ተዋረድ | ፩) የማኑ ራስ ወደታች ሁኖ ሲከደን ፤ የኑሮ ደረጃ ። |
| ተዋናዩ | ተጨዋች Actor ። |
| ተዋናዩት | ተጨዋች Actress ። |
| ተውህበ | ተ. ተሰጥዎ ። |
| ተዘጠረ | ተወዘረ ፤ ተዘፈረቀ ፤ ተጎለተ ። |
| ተዛነብ | ተ. ዛኒጋባ ። |
| ተዛና | ሐሳብ ጥሎ ተቀመጠ ። |
| ተደቃ | እየኖሆለለ ሄደ ። |
| ተደነበ | ተ. ተደረበ ፤ ተዳበለ ። |
| ተደረረ | ፈከረ ፤ ተጀነነ ። |
| ተጋን | የአትክልት ቦታ Garden ። |
| ተጥለገለገ | ተ. ተጭለመለም ። |

| | | |
|---|---|---|
| ተጥለግለግ | | Twilight |
| ተጽዕኖ | | ወፍጮ መድፊያ ። |
| ተፎለለ | | ተደሰተ ፤ ቀስ እያለ ጠጣ ። |
| ተፍነከነከ | | ተ. በጣም ተደሰተ ተቃ አኖቀኖቀ ። |
| ተናጋ | | ተ. ላንቃ ። |
| ቱማታ | | ተ. ቀጥታ ፤ በቱማታ ፤ በቀጥታ ። |
| ቱሲ | | ተ. ፈሪ ፤ ደካማ ፤ ጡርቂ ። |
| ትርክዛ | | ተ. ከዘራ ፤ መቋሚያ ። |
| ትርንትር | | ጉንፋን ሲይዝ ቀጭን ውኃ መስሎ በአፍንጫ ሚንቄረቄረው ተቃ አንጐል ። |
| ትእምርት | | ተ. ምልክት Sign ። |
| ቶርቱራ | | የበሰለ በደምብ የተቀቀለ ። |
| ቶና | | ሁለተኛው ቡና ካቦል ቀጥሎ ከበረካ በፊት ። |
| ቶፋ | | ምንቸት ፤ ትንሽ ጣራ ። |
| ችበ | ፩) | አንድ ጭብጥ (እህል ሲታጨድ በአንድ እጅ ጭብጥ የሚሞላው) ፪) ሹግ፤ ዳቦት ። |
| ችውችዋ | | ከሑራ ላይ የሚበቅል ሣር ። |

## ነ

| | | |
|---|---|---|
| ነሲብ | | ተ. ጅምላ ። |
| ነር | | ከመቄብቄቡ በፊት አጫጅ እየጣለው የሚሄደው እህል ። |
| ነበር | | ተ. ተቀማጭ ፤ እማኝ ተቃ ሃጅ ፤ መጢ ። |
| ነቀላ | | የፊት እግር ። |
| ነቅል | | ተ. ምንጭ ተቃ ዲካ ወንዝ ። |
| ነት | | የላም ነት ። |
| ነቸፈ | | በጥርሱ ከሥጋ ነከሰ ። |
| ነዶ | | (የገብስ) እስር ። |
| ነገለ | | ተ. ደሸለቀ ተቃ ለመለመ ደደቀ ። |
| ነግሀ | | አጠባብ ፡ በንጋት ጊዜ ። |
| ነፋፋ | | ተ. የረጅም ቂል ፤ ከርፋፋ ። ተቃ ብልህ ብልጥ ። |
| ናርጅ | | የሙሽሮች የራስ ቅቤ ቅል ። |
| ኔል | | ተ. ዶፍ ፤ ኀይለኛ ዝናም ። |

## ኢ. ዐ.

| | | |
|---|---|---|
| አህያ | ፩) | ግመል ፤ ተሸካሚ ፤ ቤት ውስጥ ዳር ዳሩን የሚያቋርጥ ፪) በአልጋ ዙሪያ |